ትውልድ ፈታኝ ቀውጥ !!!

“በእንቅርት ላይ ጀሮ ደግፍ” እንዲሉ፣ በድረቅ የደቀቀው ህዝባችን፥ በላሁኑ ወቅት ደግሞ በግሞቶች ሳብያ እያለቀ ነው። ሃገር ከባድ ቀውጥ ውስጥ ገብታለች። በእርስበርስ ግሞቶች ሳብያ ከድንበሩ ጀምሮ ማህሉ ድረስ ባለው ህዝባችን ላይ የሞትና የመቁሰል ላደጋዎች እየደረሱ ናቸው። በገፍ መፈናቀልና ንብረት መውደም ላብሮ እየተከተለ ነው። ግሞቱ ባልደረሰባቸው ላከባቢዎች ሞንቅና ፍርሃት ላይለዋል። ይህ እየተሰራጨ ያለው ክፉ ክስተት ማቆምያ ካልተበጀለት ሃገር-ላልባ ሊያደርገን ይችላል። ቀውጡን የፈጠረው የህወሓት/ኢህአዴግ ገዢ መደብ ለመሆኑ ላጠያያቂ ላይደለም። ይህ ሓላፊነት የማይሰማው ላምባገነን ቡድን ገና ከጅምሩ የወጠናቸው ደንባራና ስግብግብ ፖሊሲዎች እንዲሁም ላረመንያዊ የላገዛዝ ዘይቤዎች ላሁን ከምንገኝበት ላረንቋ ውስጥ ከቶናል። ላጠቃላይ ላቅጣጫው መላው ህዝቡን እርስበርስ የሚያፋጅ፥ ሃገርን በጎጥ ሞምር የሚበታትን ለመሆኑ በላራቱም መላዝናት ከሚሰማው የድረሱልን ጩኸት መገንዘብ ላያዳግትም።

ይህን ላሳሳቢ ምጽላት መቀልበስና ወደ ብሩህ ስኬት መለወጥ ላይቻልምን? ምን ቢደረግና ማን ቢያደርገው ነው ሃገራችን ከዚህ ጥልቅ ቀውጥ ማውጣት፥ ህዝባችን ደግሞ ከወረደበት መከራ ማዳን የሚቻለው? እነዚህና ተጓዳኝ የሆኑ ጥያቄዎች ለማንም ላርቆ-ላሳቢ ዜጋ ሁሉ እንቅልፍ የነሱና መፍትሄ ለማግኘትም እያነጋገሩ ያሉ መሆናቸው ይታወቃል። በየላቅጣጫው ጥረትም እየተደረገ ነው፣ ሆኖም ግን ጥረቱ ከላደጋው ላጥፊነትና ላጣዳፊነት ላንጻር ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል ይዘት ስለሌለው ላደጋው ከቁጥጥር ውሞ እንዳይሄድ በብዙ ሃገር-ወዳድ ዜጎች ዘንድ ስጋት ላለ። ይህ እጅግ ላሳሳቢ ስጋት የዚሁ ትውልድ ፈተና መሆኑ ነው። ወቅታዊና ተግባራዊ መልስም ይሻል።

ይህ “ትውልድ ፈታኝ ቀውጥ” በሚል ርእስ የቀረበው ላሞር ጽሁፍ የችግሩን ምንጭና ተከትሎ እየመጣ ያለው ላደጋ በማብራራት የመፍትሄ ላቅጣጫ ይጠቁማል፣ ከወዲሁም ሓላፊነት በሚሰማቸው ዜጎች መካከል እየተካሄደ ላለው ጥረት መለስተኛ ላስተዋጽኦ ይሆናል ብሎ ያምናል።

የችግሩን ምንጭ

በላጠቃላይ ሲታይ የሃገር ሉዓላዊነትና የህዝቡ መብት መከበር ተነጣጥለው የሚታዩ እሴቶች እንዳይደሉ ሁሉ፥ እነዚህ እሴቶች እንዲኖሩ የሚያስችል ስርዓተ-መንግስት ላለመኖሩ የሁሉም ችግሮቻችን ዋናው ምንጭ ነው ማለት ይቻላል። እስከ ላሁን ድረስም በኢትዮጵያችን የሃገር ሉዓላዊነትና የህዝብዋ መብት የሚያስከብር ስርላተ-መንግስት ተመስርቶ ላያውቅም። ለዚህም ነው ሰላም፣ እኩልነት፣ ላንድነትና ብልፅግና የራቀን፣ ፖለቲካዊ ባህላችንም ድንኪየ የሆነው። የሃገራችን ነፃነትና የህዝቧ የመወሰን መብት በጋራ በሚመሰረተው ስርዓተ-መንግስት ስር ሆኖ ተግባራዊነቱ እስካልተረጋገጠ ድረስ ለዘመናት የዘለቀውን መከራ ላያበቃና በከፋ መልኩም ሊቀጥል እንደሚችል መገንዘቡ፥ ከያዝነው ርእሰ-ጉዳይ ጋር የሚታይ ላስፈላጊና ወቅታዊ ጉዳያችን ነው።

ስርላተ-መንግስት (ስቴት) ሲባል መንግስት (ገቨርንመንት) ከሚባለው የላስተዳደር ላካል የላቀ፣ ሰፊና ዘለቄታ ያለው የላገዛዝ ዘይቤ ነው። ይህ ማለት ሰዎች ወይም ድርጅቶች ግላዊ ፍላጎታቸውን ሆን ብለው ገድበው፥ በጋራ ለሚተዳደሩበት ላስገዳጅ መዋቅር ተገዢ የሚሆኑበት ስርዓትን ይመለከታል። ዴሞክራሲ እስከ ሰፈነ ድረስ በላንድ ስርላተ-መንግስት ስር የተለያዩ እንዳውም በረካታ መንግስታት ሊፈራረቁ እንደሚችሉ የታወቀ ነው።

ስለዚህም ነው የትግላችን ስትራቴጂያዊ ዓላማ በህዝቡ ሙሉ ተሳትፎና ኣመኔታ የሚዋቀር ስርኣተ-መንግስት መመስረት ይቅደም የምንለው። ይህ ሁሉን-ኣቀፍ ስርኣተ-መንግስት የተለያዩ (የግራም ይሁን የቀኝ) ርእዮተ-ዓለም የሚያቀነቅኑ ሃይሎች በእኩልነት የሚያስተናግድ ይሆናል። በዚህ ዓይነቱ ስርኣተ-መንግስት ስር ሆኖው የተለይየ ኣቋም ያላቸው ፓርቲዎች በእኩልነት ተወዳድረው ኣብላጫ የህዝብ ድምጽ ያገኙት ወገኖች መንግስት ሊመሰርቱና ሊመሩ ይችላሉ። ይህ ሂደት ዘላቂ ሰላምና ዕድገት የኑሮኣችን ኣካል የሚያደርግ ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ የጋራ ስርኣት ኣስቀድሞ ሳይመሰረት የሚመጣ የመንግስት ለውጥ 'የጉልቻ መቀያየር' እንዲሉ፣ ቀውስን የሚያባብስ እንጂ መፍትሄ ሊሆን ከተውንም ኣይችልም። ስለዚህ የጋራው ዓላማችን የጋራ ተሳትፎን የሚጠይቀው ሁላችንን በእኩልነት የሚያስተናግድ ፍትሃዊ ስርዓተ-መንግስት መመስረት ሆኖ፣ ለዚህ በጎ ዓላማ መሳካት እንቅፋት የሚሆኑትን ሁሉ ታግሎ ማስወገድ እንደ ቅድመ ሁኔት ማየቱ የግድ ይላል።

ለዘመናት የተከማቹት ችግሮቻችን ስር የሰደዱና የተንዛዙ ቢሆኑም ቅሉ፣ በማንኛውም ዘመነ-መንግስት ችግሮቹን ለመፍታት ሙከራዎች ኣልነበሩም ማለት ኣይደለም። ሙከራዎቹ ግን በኣጭር የሚያዩ፣ በዋናነት ግላዊና ወገናዊ ስግብግብ ፍላጎቶች ያጠቋቸው ቁንፁላን ኣካሄዶች ስለነበሩ ከመፍትሄነታቸው ይልቅ ሰበባቸው እያየለ መምጣቱ ኣይካድም። የችግሮቹ ምንጭ ከኋላ-ቀር ስርዓቱ ለመሆኑ ኣከራካሪ ኣይደለም። የኣጼዎቹ ይሁን የደርጎቹ እንደዚሁም የኢህኣዴጎቹ መንግስታዊ ስርዓቶች በቅርጽ ይለያዩ እንደሆን እንጂ በይዘት ኣይራራቁም። ሁሉም የህዝቡን መብት የሚንዱ የጭቆና ስርዓቶች ናቸውና። ስለዚህም የኣስመሳይ ቡድኖች ሳይሆን የመላው ህዝብ ፍላጎትን የሚያንጸባርቅ ስርዓት ተመስርቶ፣ በህዝብና በሚፈጠረው መንግስታዊ ስርኣት መካከል የሚኖረው ቁልፍ ግንኙነት በማያሻማ ሁኔታ መስተካከል ኣለበት። ይህ ግንኙነት እስካልተስተካከለ ድረስ ከጨቋኝ መንግስታትና ከሚያስከትሉት ዘርፈ-ብዙ መከራ ኣንገላገልም ማለት ነው።

ከዚሁ ኣጠቃላይ ግንዛቤ በመነሳት ለወቅቱ ችግሮቻችንን ትኩረት ሰጥተን መፍትሄ ስንቃኝ፣ የችግሮቹ መንስኤ ከሶስት ኣቅጣጫዎች በኩል የሚመነጩ እንደሆኑ ማመላከት ይቻላል። እነሱም፣ 1ኛ/ ስልጣን ላይ የሚገኘው ህወሓት/ኢህኣዴግ፣ 2ኛ/ የውጭ/ባእዳን ሃይሎች፣ 3ኛ/ በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈው ወገን፣ እኛው ራሳችን ቢባል ያስኬዳል። እነዚህ ሶስት ክፍሎች ባንድ በኩል ራስ-ወጥ ሆኖው፣ በሌላ በኩል ደግሞ የትብብርም የፀርነትም ግኑኝነት ፈጥረው ስለሚንቀሳቀሱ ለፍትህ የሚካሄደው ትግል ረጅምና ውስብስብ እንዲሆን ከማስገደዱ በላይ ሃገራችንን ለመከፋፈል፣ ህዝባችንን ለእልቂት እየዳረገ ለመሆኑ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል።

ምናልባት እዚህ ላይ በተቃዋሚው ጎራ የሚገኝ ኣካል ለትብብራችን ችግር ፈጣሪ መሆን እንዴት ይታሰባል? የሚል እሳቤ ኣይጠፋም፣ ግን መልሱ ባጭሩ ኢህኣዴግ በቀየሰው የልዩነትና የጥላቻ ፖለቲካ መራመድ ካለ፣ ተሸፋፍኖም ይሁን በግልጽ ይከሰታልና፣ ኣሉታዊ ትብብር ይሉታል ይኸው ነው። እንግዲህ የችግሮቹን ምንጭ ባጭሩም ቢሆን ኣንድባንድ ለማየት እንሞክር፣

1ኛ/ የመጀመርያው ችግር ህወሓት/ኢህኣዴግ ሲሆን ይህ ቡድን የመሰረተው መንግስት ሽብርተኛ-ኣምባገነን ለመሆኑ የሚያከራክር ኣይደለም - ለ26 ዓመታት ተግተነዋልና። በዚህ ሽብርተኛ-ኣምባገነን መንግስት ኣማካኝነት ኣዲስ ገዢ-መደብ ተፈጥሯል። የዚህ ኣዲስ ገዢ-መደብ ኣስኳል የህወሓት ቡድን ቢሆንም ከሁሉም ብሄር-ብሄረሰቦች የተውጣጡ በኢህኣዴግ ስም የተሰባሰቡ የገዢ-መደብ ኣባላት ኣሉበት። እንደ ገዢ-መደብ ኣባላት ሁሉም ብዝበዛውና ሽብሩ ኣምባገነናዊ በሆነ መልኩ እያካሄዱት ይገኛሉ። ጭንቀታቸው ሲያይል 'ጊዚያዊ ኣዋጅ' በሚል ስም ሽብርተኛነታቸውን ያከሩታል። ጎን ለጎን ደግሞ የየብሄረሰባቸው ተቆርቋሪ በመምሰል የሌሎቹ ብሄረሰቦች ተቀናቃኝ በመሆንና ልዩነትን በማስፋት ህዝብን እርስበርሱ እያጋጨ ተዝናንተው ለመግዛት ይጥራሉ። ቀደም ሲል በኣንዋክና በኑወር ጋምቤላዎች፣ ኣሁን ደግሞ

በኦሮሞና በሶማል ዜጎቻችን መካከል የተካሄዱና እየተካሄዱ ያሉ አልቂቶች - ከብዙ በጥቂቱ - እንደ ላብነት መጥቀስ ይቻላል። ይህ ድርብ ስለት ያለበት ላስነዋሪ የላገዛዝ ዘዴ በተናጠል ይሁን በጣምራዊ ይዘቱ ጠንቅቆ ላውቆ ላልፎ መቆየት የትግል ስልቱ 'ሀ' 'ሁ' ነው።

2ኛው ችግር ባዕዳን/የውጭ ሃይሎችን ይመለከታል። ሽብርተኛ-ላምባገነኑ ኢህላዴግን በገንዘብ፣ በመሳርያ፣ በዲፕሎማሲ፣ በማፈኛ ዘዴዎች ወዘተ፣ የሚያስታጥቁት የለመደባቸው ባዕዳን ሆነው፣ ላሁን በዋናነት የላሜሪካና የእንግሊዝ መንግስታት ቀጥሎ ደግሞ የላውሮፓና የቻይና መንግስታት በፀረ-ህዝብ ቅንብሩ ተሳታፊዎች ናቸው። ሁሉ ጊዜ የሃገርን ልዕልና፣ የህዝብን ላመኔታ መሰረት ያደረገ መንግስት እንዲኖር ላይፈልጉም፣ ለስትራቴጂያዊ ዓላማቸው ዕንቅፋት ላድርገው ይቆጥሩታልና። የሃገሩንና የህዝቡን መብት ቅድሚያ የሚሰጥና የሚያስከብር መንግስት የማይፈልጉ ለመሆናቸው ከታሪክም ሆነ ከወቅታዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ መገንዘብ ላይከብድም።

ከዓለምላቀፋዊው ግኑኝነት ተነጥሎ መኖር ላይቻልምና፣ ታድያ እነዚህ ባዕዳን ሃይሎች መቼ እና በምን ሁኔታ ላይ ስንሆን ነው በጊዚያዊነትም ቢሆን ሊተባበሩን የሚችሉ ብሎ ከታሪክም ይሁን ከወቅታዊ ተጨባጭ እውነታ ላንባር በቅጡ መመርመር ያስፈልጋል። ለዚህ ላጭር መልሱ የተበታተኑት ሓይሎችን በማሰባሰብ፣ ህዝባችንን ላደራጀትና ከጎኑ ተሰልፈን የምር ሓይል ሆነን ስንገኝ ብቻ ነው። ያኔ ብቻ ነው የምር የሚያዳምጡን።

3ኛው ችግር በተቃዋሚ ጎራ የተሰለፈው ወገን ማለት 'እኛው' ራሳችን ጨምሮ የሚመለከት፣ ተበታትኖ የመታገል ላባዜ ነው። ካፍንጫችን ያልራቀው እውነታ እንድሚያሳየው፣ ተበታትነን እየታገልን ላንድባንድ እየተመታን ይኸውና 26 ዓመታት ተሰቃይተናል። ይህ የትርምስ ጉዞ ላሁንም ላላበቃም። የሚያበቃበት መንገድ መፈለግ እንደ ቀዳማዊ ስራ፣ ላልያም እንደ ቅድመ-ሁኔታ ታይቶ ርብርቦሽ ሊደረግበት የሚጠይቅ ስትራቴጂክ ጉዳይ ነው። የተበታተኑት የእኩልነት፣ የላንድነት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ ሓይሎች ካልተሰባሰቡና ተደራጅተው ትግሉን ካልመሩት ኢህላዴግ ሊወገድና የሰርዓት ለውጥ ሊመጣ ከተውንም ላይችልም። በዚህም ሳያበቃ፣ የቁልቁሉ ጉዞ ተፋጥኖ ጭራሽ መግታት የማይቻልበት ላደጋ ሊከሰት ይችላል። በላራቱ የሃገራችን መላዝናት እየተካሄድ ያለ ላሳዛኝ እልቂት የሚያመላክተው ይኸው መራራ ሓቅ ነው።

ይህ ስር የሰደደው የመከፋፈል በሽታ የትግላችን ነቀርሳ ከመሆኑ ባሻገር፣ ህወሓት/ኢህላዴግ ስልጣን ላይ ሲወጣ ጀምሮ የመጣ ላድርጎ ማየቱ ደግሞ ሌላ ስህተት ሲሆን፣ ሰር-ነቀሉ መፍትሄ የስርዓት ጉዳይ መሆኑ ኮለል ብሎ እንዳይታይና እንዳይጨበጥ እንቅፋት መደቀኑም ላልቀረም። እስካሁን የነበሩን ስርዓቶች በገቢር ተመሳሳይ እንደሆኑ ከላይ መጥቀሳችን ለዚህ ነበር። በርግጥ ህወሓት/ኢህላዴግ ክፍፍሉ በላዲስ መልክ ላቀነባብሮና ሕጋዊ ልባስ ሰጥቶ መተዳደርያው ደንብ ላድርጎታል። ይህ ድርጊት ሃገራች ወደ ባሰ የመከፋፈል ላደጋ እንድታሽቆለቁል ላድርጓታል። ላደጋው ደግሞ እላይ እንደተገለጸው በጣም ላሳሳቢ መሆኑ ወቅታዊ ጭብጦች ያስረዳሉ።

መዘዙ፣

የችግሮቹ ምንጭ ከሶስት ላቅጣጫ መሆኑ ካየን ዘንድ፣ ይህን ተከትሎ እየተገከባለለ በመምጣት ላይ ያለው ላደጋስ የት ሊያደርሰን ይችላል? ላደጋው ከመድረሱ በፊት መግቻ ሊበጅለት ላይቻልምን? ብሎ መጠየቁ የወቅታዊው ችግሮቻችን መፍትሄ ከመፈለግ ላንጻር ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ላደጋው ተመልሶ ላይመጣ ዘላቂ ስርዓትና ድንብ ለማነጽ ስለሚረዳ ጥያቄው እጅግ ላስፈላጊ ሆኖ እናገኘዋለን።

ያለምንም ጥርጥር፥ የተቀሰቀሱት ግጭቶች ለሁሉም ወገን ኪሳራ እንጂ ትርፍ ላላመጡም፣ ላያመጡምም። ላብዛኛው ኪሳራ ደግሞ መተኪያ ላይገኝለትም፣ መዘዙም ለቀጣይ ትውልድ ሊተርፍ ይችላል። እየተንከባለለ ብሎም እያየለ በመምጣት ላይ የሚገኘው፥ ሁሉን ላውዳሚ ላደጋ ስፋቱና ጥልቀቱ ለመገንዘብ ይረዳ ዘንድ እንሆ ባለፉት ላስር ዓመታት (ከ 2001 እስከ 2011 ዓ/ም/ፈረንጅ ባለው ጊዜ ብቻ) ባለሙያዎች ከዘገብዋቸው ግጭቶችና መዘዛቸው ለናሙና ያህል ላጠናቀረን ያዘጋጀነውን ቀጥሎ ማየት ይቻላል።

ዓ/ም/ፈ	የየአካባቢ ግጭት	የሞተ ሰው ብዛት
2001	ቦረና ከ ጌሪ	62
2002	ከረዩ ከ ላፋር	56
2002	ኑወር ከ ላኝዋክ	60
2003	ኦሮሞ ከ ኦጋዴኒ	18
2004	ላኝዋክ ከ ደገኞች	200
2005	ላፋር ከ ኢሳ	83
2006	ጉጂ ከ ቦረና	125
2007	ኒያንጋንቶም ከ ካሪ	?
2008	ደራሻ ከ ኮንሶ	33
2009	ካፊኞ ከ ኦሮሞ	? (70,000 ተፈናቃይ)
2010	ጅካኒ-ኑወር ከ ሉዎ-ኑወር	? (32,000 ተፈናቃይ)
2011	ኦሮሞ ከ ጉሙዝ	? (1800 ተፈናቃይ)

ምንጭ፥ የተ.መ.ድ.-ኢሪን እና የኢ.ሰ.መ.ኮ. (ጥንቅሩ የቆሰሉ፥ የወደመ ንብረትና ሁሉጋ የሞቱና የተፈናቀሉ ላይጨምርም)

ይህ ላሁን በምስራቅና በሰሜን ክፍላተ ሃገራችን የተቀሰቀሰው ግጭት ላዲስ ክስተት ሆኖ መታየት ላይኖርበትም፣ እላይ ለናሙና ከተጠቀሱት ግጭቶች የቀጠለ እንጂ። ህወሓት/ኢህላዴግ ስልጣን ላይ ወጥቶ፥ ከፋፋይ ፖሊሲውን የተግባር መመርያ ሲያደርገው ጀምሮ የነበሩ ግጭቶች ናቸው፣ ላሁንም ሃገራችንን እየናዱና ህዝቦቻችንን እያጨረሱ ያሉት። ላያርገው እንጂ እነዚህ የተዳፈኑ ግጭቶች ባንድ ወቅት ቦግ ብለው ቢነሱ፣ የሚተርፍ ሃገር፥ የሚድን ህዝብ ይኖረናል? "ላያርገው" ተብሎ የሚታለፍ ጉዳይ ደግሞ ላይደለም። የላምባገነኑ ህወሓት/ኢህላዴግ የተግባር መመርያ ነውና ይህ መሰሪ ገዢ መደብ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ "ላይመጣምን ትተሽ፥ ይመጣልን . . . " ብናስብና ላደጋው ሳይቀድመን ለመፍትሄው ብንረባረብ ለሁሉም ይበጃል።

የመፍትሄ አቅጣጫ፥

ህዝብ የለውጥ ማዕበል ሊሆን ከተፈለገ አሰባሳቢና አቅጣጫ አመላካች ፈታውራሪ ያስፈልገዋል። እንዲሁ ጥግ ይዞ "ህዝቡ ምን አለ? ለምን አይነሳም?" ብቻ ማለት "ውጊያ ላይ ያልዋለ፥ ስለታም" እንዲሉ አጉል ብልጣብልጥነት አልያም የዋህነት ነው። ህዝቡ እንደሆን በተናጠል እየተነሳ በተናጠል እየተመታ፥ እየቆሰለና እየደማ ነው ያለው። የተበታተነ ሓይል ደግሞ እርባና እንደሌለ ይኸውና የ26 ዓመታት ውጣውረድ ግልብጭ አድርጎ አሳይቶናል። የተገኘ ለውጥም የለም። ለውጥ ስንልም፥ አላይ እንደተጠቀሰው ከመንግስት ለውጥ በእጅጉ የላቀ፥ የስርዓት ለውጥ ለማለት እንደሆነ ከወዲሁ ሊታወቅ ይገባል።

ይህ ከባድ ሓላፊነት የስርዓት ለውጥ ፈላጊዎች በሆኑ በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪል ማሕበራት ትከሻ ላይ የወደቀ ለመሆኑ ላጠያያቂ አይደለም። ይሁንና ይህ ሰፊና የተዘበራረቀ ሓይል በተለምዶ ተቃዋሚው ጎራ የተሰኘው፥ በአንድ የጋራ ዓላማ የተጣመረ ሳይሆን የተበታተነ ለመሆኑ ቤተ እምነቶቹ ሳይቀሩ ይመሰክራሉ። አንዳንዶቹም ህወሓት/ኢህአዴግ የቀየሰውን የመከፋፈል ስንጥቆች እየተከተሉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ችግሩን በማባባስ ላይ የሚገኙ እንዳሉ መታወቅ አለበት። ይህ አዝማምያ ለጋራ ትግሉ ክፉ ነቀርሳ ከመሆኑ አልፎ፥ ውሎ አድሮ የሚያስጠይቅ የርስበርስ ጦርነት ዘርም እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ችግርን ፈቺ መሆን የነበረበት ሓይል እራሱ ችግር ሆኖ ሲገኝ፥ ችግሩ ይፈታል ብሎ ማሰብም ከቶ አይቻልም። ትርጉም ያለው የለውጥ ሓይል መፍጠር ከተፈለገ በየመስኩ የሚገፀባረቁት የጥበትም ይሁኑ የማንአህሎብኝነት ከፋፋይ አመለካከቶች ያለይሉኝታ ማስወገድ፣ ከፋፋይ አጥሮችን መስበርና የተበታተነው ህዝባዊው የወገን ሓይል በየመድረኩ ማገናኘትና መልክ ማስያዝ የግድ ይላል።

ከዚህ አይታ በመነሳት፥ አሁን ከፊታችን ተደቅኖ ካለው አደገኛ ሁኔታ አኳያ መወሰድ ያለባቸው አጣዳፊ እርምጃዎች ምንድን ናቸው? ለሚለው አንገብጋቢ ጥያቄ ወሳኝ አቅጣጫ የሚያስይዙን መልሶች የሚከተሉትን ናቸው ማለት ይቻላል።

ሀ/ የተለያየ የታሪክ፥ የፖለቲካ፥ የሃይማኖት፥ የብሄረሰብ፥ የድርጅት ታማኝነት፥ የትግል ስልት . . . ወዘተ ልዩነት ይኑረን አይኑረን፣ የአንድን ሃገር ዜጎች እስከሆን ድረስ በዚች ሃገር ላይ የሚደርሰው አደጋ ሁላችንን የሚያቆስል በመሆኑ፥ ልዩነታችን በጋራ በምንመሰርተው ስርዓት ውስጥ በአግባቡ ለማስተናገድ በይደር አቆይተን፣ አሁን ከፊታችን ለተደቀነው ሃገራዊ አደጋ ለማምከን በጋራ መቆም፣

ለ/ ሁሉን የፖለቲካና የሲቪል ድርጅቶች የሚወክልና ወቅታዊ ስልጣን የተጎናጸፈ አስተባባር አካል ማቋቋም። የዚህ አካል አምሳያ ሃገር-ቤትም ውስጥ እንዲቋቋም የሚቻለውን ሁሉ ማድረግና ሁለቱም አካላት ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማስቻል፣

ሐ/ ይህ ተነሳሽነት ማን ይያዘው ለሚለው (በኢትዮጵያውያን ዘንድ አወዛጋቢ የሚሆን) ጥያቄ፣ ካጋጠመን ጊዜ የማይሰጥ ችግር አንጻር ሲታይ መልሱ ***አቅም ያለው* ወገን ቢባል የሚያስኬድ ነው። ምክንያቱ ይህ የጋራ ሃገራዊ ጉዳይ፥ በጋራ ተሳትፎ የሚደረሱ ውሳኔዎች መሰረት አድርጎ የሚገባደድ ወቅታዊ የቤት ስራ ነውና። በዚህ ጉዳይ ቀደም ብለው ተነሳሽነት የወሰዱ ሓይሎች ካሉ ተሰባስበው ስምሪቱን ቢያጠናክሩ ለተቀላጠፈ ውጤት ማግኘት አስተዋጽኦ እንዳለው መገንዘብ አይከብድም።**

መ/ ማንኛውም ዜጋ - በድርጅት ይካተት አይካተት - ይህን ሃገር-አድን የሆነው የጋራ የመፍትሄ አቅጣጫ እግቡ እንዲደርስ፣ በየአቅራቢያው በሚገኘው ድርጅት አመካይነት ተግባራዊ አስተዋጽኦ ማድረግ ይጠበቅበታል። ትውልድን የሚፈታተን ቀውጢ ወቅት ውስጥ እንገኛለን ስንል ይህንኑ ለጋራ የመጣው አደጋ የጋራ መፍትሄ እንደሚሻ በመገንዘብ ነው።

ይህ ኣካሄድ በመጪው ስርዓት ተጠቃሚ የሚሆነውን ወገን ሁሉ ኣሰባስቦና ኣደራጅቶ ኣደጋውን ከቀለበሰ በኋላ፣ የመጪውን ስርዓት ይዘት በጋራ የሚወስንበት የጋራ መድረክ ይሆናል የሚል እምነትም ኣለን።

ለማጠቃለል ያህል፣ ህዝባዊ መሰረት ሳይኖረው፣ ኣንድ የለየለት ኣፋኝ ቡድን መንግስታዊ ስልጣን ይዞ በሃገርና በህዝብ ላይ ገደብ-ኣልባ በደል እየፈፀመ ለ26 ዓመታት ሊዘልቅ የቻለው ህዝብ ስላልተቃወመው ወይም ድርጅቶች ስላልታገሉት ኣይደለም። ህዝቡ ይቃወማል፣ በርካታ ድርጅቶቸም 'ይታገላሉ'፣ ነገርግን ትግሉ ቅደም-ተከተሉን ኣሳምሮ ሳያስቀምጥና ኣስተባባሪ ማዕከል ሳይፈጥር፣ በተዘበራረቀ መልኩ በመካሄዱ እግቡ ሊደርስ ኣልቻለም። ይህ ግድፈት ኣደጋውን እያባባሰ ጫፍ ላይ በማድረሱ፣ የዚህ ግድፈት ባለቤት ማለትም ያለው ትውልድ ተጠያቂ መሆኑ ባይቀርለትም፣ ኣደጋው ሞራሽ ከቁጥጥር ውጭ ሳይሆን ዜጋዊ ግዴታው ሊወጣ ይገባል።

የሆነሆኖ ኣሁን ግፍኦች በመላ ሃገሪቱ እየተዛመቱ ናቸው። ህወሓት/ ኢህኣዴግ ከየኣቅጣጫው በሚሰነዘሩት ህዝባዊ ተቃውሞዎችና፣ ከውስጡም በራሱ በቅራኔዎች የተዋከበበት ወቅት እንገኛለን። ይህ ክስተት ወዴት እንደሚያመራ እሩቅ ሳንሄድ ከጎረቤቶቻችን መገንዘብ እንችላለንና ኣደጋው ሳይቀብረን፣ ተባብረን መፍትሄው እውን የምናደርግበት ኣቅጣጫ ተሎ እንያዝ እንላለን።

ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!

ኣረጋዊ በርሄ

ezanareg@hotmail.com